# ግንቦት 7 እና የኢትዮጵያ አንድነት[1]

ብርሃኑ ነጋ

## መግቢያ

በመጀመሪያ ይህን ስብሰባ ያዘጋጀው የኢትዮጵያውያን ህዝባዊ ፎረም ድርጅታችንን ግንቦት 7ትንና ድርጅታችን አባል የሆነበትን ጥምረት ለነጻነት፤ ለፍትህና ለእኩልነትን (ጥምረት) ወክዬ በዚህ ስብሰባ እንድገኝ ስለጋበዘኝና፤ በዚህ ስብሰባ ለመሳተፍ ፈቃደኛ ሆናችሁ እዚህ ለተገኛችሁ ወገኖቼ የከበረ ምስጋናየንና ሰላምታየን አቀርባለሁ።

በእንዲህ አይነቱ ስብሰባ በተገናኘን ቁጥር እንዲህ አይነቱን አጋጣሚ ትንሽም ቢሆን የረባ ስራ ሰርተንበት መሄድ ይኖርብናል ብዬ አምናለሁ። ጊዚያችን፣ ጉልበታችን፣ ገንዘባችንና ስሜታችንን ፈሰስ አድርገን እንዲህ አይነቱን ስብሰባ ስናዘጋጅ አላማው ትንሽም ቢሆን የፓለቲካ ሰዎች ነን፤ የሁሉንም የሃገሪቱ ህዝብ ወይም በተወሰነ ክልል ያለው ህዝብ ስቃይና መከራ ከምር ያሳስበናል በምንል ሃይሎች መሃል የጋራ መግባባት ለመፍጠሪያነት እና ትንሽም ቢሆን በመሃከላችን ያለውን ያለመግባባትና ብዥታ ለማጥሪያና በሁላችንም ላይ ከተከመሩብን ተራራ የሚያካክሉ ብሄራዊ ችግሮች የተወሰነውን ለማቃለል ትንሽ እገዛ የሚያደርግ ስብሰባ ሊሆን ይገባዋል የሚል እምነት አለኝ።

ከዚህ እምነት በመነሳት ለእንዲህ አይነቱ ስብሰባ ስጋበዝ ጊዜ ወስጄ ለጉዳዩ በቂ ትኩረት በመስጠት አስብበታለሁ። በእንዲህ አይነቱ ስብሰባ የምናደረገው ንግግር የምንገጥመው ሙግትና ክርክር የምንጠመድበት ውይይት በዚህ አዳራሽ ውስጥ ታጥሮ የሚቀር ሳይሆን ከዚህ ስብሰባ አዳራሽ ውጭ ወደሚገኙ በሽዎችና በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ወገኖቻችን ጆሮ የሚደርስ፣ በጎም ክፉም መዘዞች ያሉት እንደሚሆን ስለማውቅ በሚገባ መዘጋጀቱን እመርጣለሁ። ለዚህም ነው፥ በበርካታ ስብሰባዎች ላይ የማደርገውን ንግግር በጽሁፍ ማቅረብ የምመርጠው። በጽሁፍ ማቅረቡ ሌላም ጠቀሜታ አለው። ይህ ስብሰባ ካለቀ በኋላ በስበሰባው ያልተገኙ ወይም ስብሰባውን በሌሎች ሚድያዎች ለመከታተል ያልቻሉ ወገኖቻችን በዚህ ስብሰባ እኔም ሆንኩ የግንቦት7 ንቅናቄ የሚያቀርባቸውን ሃሳቦች በስማ በለው ሳይሆን በቀጥታ ማንበብ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠሩ፤ ጠባብ ለሆነ ግላዊና ቡድናዊ ጥቅም ሲሉ ከንግግሮቻችን መሃል ነገሮችን ከማእቀፋቸው እያወጡ ወይም ያልተባለውን ተብሏል በማለት በማህበረሰባችን ውስጥ ውዥንብርና ሁካታ ለመፍጠር ቆርጠው የተነሱ አካላትን መሄጃ የሚያሳጣ ይሆናል።

---

[1]ኖቬምበር 12፣2011 ዓ.ም በሲያትል ከተማ "የኢትዮጵያውያን ህዝባዊ ፎረም " ባዘጋጀው ስብሰባ ላይ የቀረበ።

በጽሁፍ የማቀረበው የዛሬው መልዕክቴ ዋናው ትኩረቱ ከሃገር፣ ከዜጎች እና ከህዝቦች አንድነት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ይሆናል። በዚህ ርእስ ስር የማነሳቸው ጉዳዮች በዋንኛነት የግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በአንድነት ጥያቄ ላይ ያለውን ግንዛቤና አቋም ምን እንደሆነና ለምን ይህን ግንዛቤና አቋም እንደያዘ ለማሳየት ነው። ይህን ርዕስ የመረጥኩት ይህ ጉዳይ በሃገራችን ፖለቲካ ውስጥ ትናንትም ዛሬ መሰረታዊ ጥያቄ በመሆኑ ነው። ዛሬም እንደትናንቱ በአንድነት ጉዳይ ላይ በህብረተሰባችን ውስጥ ያለው አመለካካት ከውንዥንብር የጠራ አይደለም። ይህ ውዥንብር የሃገራችን ህዝብ፣ በወያኔ የተጫነበትን ዘረኛ የሀገር ውስጥ የአፓርታይድ አምባገነናዊና ዘራፊ ስርአት በጋራ ትግል አስወግዶ በአንድነት መብቱን አስከብሮ ሰላም አግኝቶ እያዋረደው ካለው ድህነት ራሱን አላቆ በአለም ህብረተሰብ ፊት አንገቱን ቀና አድርጎ እንደሰው የሚታይበት ሁኔታ እንዳይፈጠር እያደረገ የሚገኝ ታላቅ እንቅፋት ነው የሚል እምነት አለኝ። የማደርገው ንግግር ትንሽም ቢሆን ይህን ውዥንብር በማጥራት ብዙዎቻችን በአንድነት ጉዳይ ላይ አይን ለአይን እንድንተያይ ለማድረግ ያግዛል ብዬ አምናለሁ። ለግልጽነትና በዚህ ስብሰባ ውስጥ ለምናደርገው ውይይት እንዲረዳ ንግግሬ በተለያዩ ሶስት ንዑስ ርዕሶች ከፋፍዬ አቀርባለሁ።

የመጀመሪያው ንኡስ ርእስ የአንድነት ጉዳይና የግንቦት 7 ንቅናቄ የሚል ይሆናል። በዚህ ርእስ የግንቦት 7 ንቅናቄ በድርጅታዊ ፕሮግራሙና በንቅናቄው መተዳደሪያ ደንብ (bylaw) ውስጥ አንድነትን በሚመለከት ያሰፈረውን የንቅናቄውን እይታና አቋም በአጭሩ አቀርባለሁ። ይህን በማድረግ የግንቦት 7 ንቅናቄ በአንድነት ጉዳይ ላይ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ የሚያንጸባርቃቸውን አቋሞችም ይሁን በተጨባጭ የሚፈጽማቸውን ድርጊቶች ከምን እንደሚመነጩ ምክንያታቶቹም ምን እንደሚሆኑ ለሁሉም ግልጽ ማድረግ ይቻላል ብዬ አምናለሁ።

በሁለተኛው ንኡስ ክፍል የማተኩረው በአንድነት ጥያቄ ዙሪያ የሚነሱ፣ ግን ዛሬ ያለንበትን የወል ወይም የጋራ አዋራጅ ሁኔታ በመቀየር ብሎም የወደፊቱን ትውልድ ከውርደት ውርስ ለማዳን ምንም ፋይዳ የማይኖራቸውን ጉዳዮች በማንሳት በአንድነት ጥያቄ ውይይታችን ፊት እንቅፋት ሊሆኑ ይችላሉ ብዬ የማስባቸው ጉዳዮች ላይ ይሆናል። በዚህ ክፍል የማቀረበው ገለጻ በጽሁፍ የቀረበ ታሪክን ሃቅንና እውነትን፣ የሚያጣቅስ ቢሆንም አቀራረቤ አየር ላይ የተንሳፈፈ አብስትራክት ወይም አካዳሚያዊ እሰጣ አገባ አይሆንም። ሁላችንም በጋራ ለገባንበት ተጨባጭ ችግር ተጨባጭ መፍትሄ ሊሰጥ በሚችል እይታ የማቀረበው ይሆናል። ይህ ክፍል ቀደምቶቻችን ዘመናዊ ሃገርና መንግስት ለመገንባት ባደረጉት ጥረት የገጠሟቸውን ድልና ፈተናዎች የምፈትሽበት እንዴትም ከዘመናዊ ሃገርና መንግስት ምስረታ ድሎች የበለጠ ፈተናዎቹ የበዙ ሆነው ለትውልድ መተላለፍ እንደቻሉ የማሳይበት ይሆናል። ከዚህ ፈተና

ለመውጣት በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ማናችንም የፍጹም ሃቆች ወይም እውነት (absolute truth) ጌቶች መሆን እንደማንችል በተለይ የታሪክና የማህበራዊ ሃቆችና እውነቶች እንደ ሂሳብና ሳይንስ እውቀቶች ሁላችንም የግድ መቀበል የሚገባን ሳይሆኑ በውይይት በድርድርና ስምምነት የምንደርስባቸው እውነቶች/ሃቆች (negotiated truth) እንደሆኑ በተጨባጭ ምሳሌዎች ለማሳየት የምሞክርበት ይሆናል። ይህን አለመረዳት በማያስፈልግና ችግራችንን ለመፍታት በማያስችል አቅጣጫ ብዙ የግዜና ጉልበት ግብአት እንዳባከንን የሚጠቁም ይሆናል። በዚህ አቀራረብ አምክህኖን (reason/rational) ከፖለቲካ እያራቅን በስሜት ብቻ የምንነዳበት ሁኔታ ውስጥ ስንወድቅ፣ እንዴት መደማመጥ እንደሚጠፋ፣ እንዴት ሊያቀራርቡን ከሚገቡ በርካታ ጉዳዮች ይበልጥ የሚያለያዩን ጉዳዮች እየሰፉ የሚመጡ መሆኑን ለማሳየት ጥረት የማደርግበት ይሆናል። አቀራረቤ ሊያስማሙን የሚችሉ ብዬ የማስባቸውን ከአንድነት ጉዳይ ጋር የተያያዙ መሰረታዊ ጉዳዮች ግልጽና በማያሻማ ቋንቋ በመሰንዘር እያንዳንዳችን በቀና መንፈስ እንድናሰላስላቸው መጋበዝ ይሆናል።

በሶስተኛው ንኡስ ክፍል የማቀረበው ጉዳይ የአንድነት ፈተናዎቻችንን ለማለፍ መፍትሄው ምንድነው? በሚለው ጉዳይ ላይ ያተኩራል። ይህ ንኡስ ክፍል አጭር ነው። በዚህ ንኡስ ክፍል የማነሳው ነጥብ የአንድነት ፈተናዎችን ለማለፍ ኣመርቂና ፍቱን መፍትሄው ምን እንደሆነ መጠቆም እንኳን ቢያቅተን፣ በተለይ ባሁን ዘመን፣ በተለይ ደግሞ ሃገራችንና ህዝቧ ካሳለፉት የቅርብ ግዜ ተመክሮ በመነሳት፣ የአለም አቀፍና አካባቢያዊ ሁኔታዎችን በማጤን መፍትሄ ለመሆን የማይችሉ ነገሮች ለማወቅ መቸገር የለብንም እላለሁ። በዚህ ረገድ እያወቁም ሆነ ካለማወቅ በዚህ ዘመንና ወቅት ለአንድነታችን ፈተና መፍትሄ የማይሆን መድሃኒት የሚያዙትን ዶክተሮች መድሃኒታቸው ጊዜው ያላለፈበት (expire ያላደረገ) መሆኑን እንዲያስቡበት የምሞግትበት ይሆናል።

ማጠቃለያዬ የሚያተኩረው ሃገራችንም ሆነ ህዝቦቿ የገበቡበትን የአንድነት አደጋና ፈተና ለመወጣት የግንቦት 7 ንቅናቄ ምን መደረግ አለበት ብሎ እንደሚያምን ምንም እያደረገ እንደሆነ በአጭሩ የሚገልጽ ይሆናል። እንደመንደርደሪያ ይህን ያህል ካልኩኝ የመጀመሪያ ወዳልኩት ንኡስ ክፍል ልመለስ።

## 1. የአንድነት ጉዳይና የግንቦት 7 ንቅናቄ

ከንቅናቄያችን የድርጅት ፕሮግራም ተጨምቆ የተወሰደውና በግንቦት 7 የአባላት መተዳደሪያ ህገ ደንብ ውስጥ በመግቢያነት ወይም እንደ (preamble) በተቀመጠው ክፍል ንቅናቄውና የንቅናቄው አባል የሆኑት

በሙሉ የሚገዙበትን የአንድነት አቋም በግልጽና በማያሻማ ቋንቋ አስፍሮታል። የንቅናቄያችን ህገ-ደንብ የአንድነት አቋማችንን ለመግለጽ ሲንደረደር እንዲህ በማለት ይጀምራል።

*"ለብዙ ዘመናት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከተገዥነት አልፎ በዜግነት ደረጃ የታየበት ጊዜ ያለመኖሩን፣ከገዥዎች ፍላጎት ውጭ በማህበራዊ፣ በፖለቲካና በኤኮኖሚ ዘርፎች ውስጥ ገብቶ በፍላጎቱ ሳይወስን፣ገዥዎቹ የሚፈጽሙትን በጎም ሆነ ክፉ ነገር ያለ ውዴታው ሲቀበል የኖረ መሆኑን፣*

*ሕዝቡ ይህንኑ የአገዛዞቹን አድራጎት በመቃወም ለመለወጥና የሚፈልጋቸውን ጥቅሞችንና መብቶችን ለማስከበር አንዳንድ ጊዜ በሀገራዊ፣ ሌላ ጊዜ በክልላዊና በዘር /በዘውግ መልክ፣ አንዳንዴ በተበጣጠሰ፣ሌላ ጊዜ በተቀናጀ መንገድ ሲያደርገው የቆየው ትግል በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ መሆኑን፣*

*ሕዝቡ ገዥዎች በቸርነታቸው ከሚወረውሩለት የመብትና የደህንነት ፍርፋሪ ውጭ በዜግነቱ ሊጠይቃቸው የሚገቡ መብቶች እንደሌሉ ተደርጎ መቆጠሩ አሁን ባሉ ገዥዎች ተጠናክሮ እየቀጠለ መሄዱን፣*

*በዚህም ዛሬ በአገራችን ራሱን ከተገዥነት አላቆ በዜግነት ሙሉ መብቱ እንዲከበርለት የሚፈልግ ሕዝብ በአንድ በኩል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ይህንኑ መብት ለማክበር ፈቃደኛ ያልሆነ አገዛዝ በመኖሩ፣"*

እያለ ይንደረደራል።

እነዚህ ንኡስ ምእራፎች እንደሚጠቁሙት የግንቦት 7 ንቅናቄ የሃገራችን መሰረታዊና ወይም ዋንኛ ችግር ቀድሞም፣ አሁንም ከዜጎች ሙብት አለመከበር ጋር የተያያዘ እንደሆነ የሚገነዘብ መሆኑን ነው። ከዛም አልፎ ዜጎች ይህን ሙብት ለማስከበር አንዳንዴ በአንድነት በሌላ ጊዜ በክልል፣ በዘርና፣ በዘውግ ላይ የተመሰረተ ትግል ያደርጉ እንደነበር በማተት የሙብት ማስከበር ትግላችን ሳይቀር የተለያዩ አደረጃጀቶች እንደነበሩት ይህ የጀርባ የትግል ታሪካችን አንድ ወጥ ሁሉንም ያካተተ ትግል የማድረግ ፍላጎታችንን ወደፊትም ቢሆን የሚፈታተን ሃቅ እንደሆነ የጠቆመ ነው። በህብረብሄር ደረጃ የተመሰረቱ ድርጅቶች እንኳን ሳይቀሩ በውስጣቸው በዘውግ የተደራጁ ንዑስ ድርጅቶች ይፈጥሩ እንደነበር የሚታወቅ ነው።

ይህም ሆኖ ባለንበት ሁኔታ የዜግነት መብት መከበር ጉዳይን የሃገሪቱ ዜጎች በአንድነት የሚስማሙበትና በጋራ የሚያምኑበት ጉዳይ መሆኑን በማተት (ለዚህ እምነታችን መነሻ ራሱ ለንቅናቄያችን ሰምና መፈጠር ምክንያት የሆነውን የሃገሪቱ ዜጎች በአንድነት ለዜግነት መብታቸው በጋራ ቆመው የነበረበትንና ወያኔን አስበርግጎ በህዝብና በሃገር ላይ እኩይ ድርጊቶች እንዲፈጽም ያደረገውን የግንቦት 7 1997 ሃገራዊ ምርጫ ተመክሯችንን ነው።) ይህ የዜግነት መብት መከበር ጥያቄ እየፈጠረ ያለው የጋራ የዜጎች የአመለካከትና ወደፊትም ሊመጣ የሚችል የተግባር አንድነት ያሰጋው የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ በስልጣን ለመሰንበት ሲል የሚሸርበውን ከሃገር አንድነት ብቻ ሳይሆን ከሃገሪቱ ህልውና ጋር የተሳሰረውን ሴራና መፍትሄውን በሚመለከት የመተዳደሪያ ደንባችን መንደርደሪያ እንዲህ እያለ ይቀጥላል።

*"ይህ ሁኔታ ያሰጋው አምባገነኑ አገዛዝ ሕዝባችንን ለመበታተን መሞከሩ ብቻ ሳይሆን፣ የአገራችንን ዳር ድንበር ለአፈና በድጎማነት እየሰጠ፣ ሕልውናዋ ከመቼውም ይበልጥ አደጋ ውስጥ እንዲወድቅ እያደረገ የሚገኝበት ወቅት ላይ በመድረሳችን፣*

***ባለጋራንና ደጋፊዎችን ከማስበርገግ ይልቅ የማቅረብን አስፈላጊነት መሠረት** አድረገን በመነሳት በሥልጣን ላይ ያለው አገዛዝ የፈጠረውን መርዘኛ የዘረኛ ፖለቲካ በማጥፋት በአንድነትና በእኩልነት የዘርና የሃይማኖት አድሎ የሌለባትን ኢትዮጵያ መገንባት ከመቼውም ይበልጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣*

*የኢትዮጵያ ሉዐላዊ አንድነትን ከተቀበሉና ከሚቀበሉ፣ በአገራችን የፖለቲካ ጉዳይ ያገባናል ብለው ከሚንቀሳቀሱ ከማናቸውም ፓርቲዎች ጋር በህብረት በመታገል በሥልጣን ላይ ያለውን አገዛዝ በማውረድ በቦታው ሁሉም ዜጎቿ ከግለሰብ መብት ጀምሮ በእኩል የሚታዩባት ሃገር መገንባት ተገቢ በመሆኑ፣*

*አገርን ከጨቋኞችና ከአፋኞች መዳፍ አውጥቶ፣ በቦታው ነጻ የሆነ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚታይባት፣ የተለያዩ ቋንቋዎቻችን፣ ባህሎቻችን፣ እምነቶታችን የውበታችን መገለጫዎች እንጂ የመለያየታችን መሠረት ያለመሆናቸው የሚንጸባረቅባት፣*

*የአንድ ሰው አንድ ድምጽ የዴሞክራሲ መርህና ሁሉም ዜጋ በህግ ፊት እኩል መሆኑን የተቀበለ የሕግ የበላይነት እምነት የሚሰፍንበትንና ተግባራዊ የሚሆንበትን፣ ዲሞክራሲያዊ የመንግሥት አስተዳደር ለማምጣት የተቋቋመው የግንቦት7 የፍትህ፣ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ መሥራች አባላት አውጥተውና አውርደው”*

የንቅናቄውን መተዳደሪያ ድንብ አባላቱ አጸደቁት ይላል።

ከዚህ በላይ የጠቀስኳቸው ቁምነገሮች፣ የግንቦት 7 ንቅናቄና አባላቱ የሃገርና የህዝብ አንድነት ብቻ ሳይሆን የሃገሪቱ ህልውና ሳይቀር ወያኔ ስልጣን ላይ እስካለ ድረስ ትልቅ አደጋ ላይ እንደሆነ የሚያምኑ መሆናቸውን የሚያሳዩ ናቸው ። ከወያኔ በላይ በአንድነታችንና በህልውናችን የላቀ አደጋ እየፈጠረ ያለ ሌላ ሃይል እንደሌለ ነው። ከወያኔ ውጭ የሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ በአንድነት ጥያቄ ላይ ከእኛ ጋር ተመሳሳይ አመለካከት የሌላቸውም የፖለቲካ ድርጅቶች ሳይቀሩ፣ ዛሬ በሃገራችን አንድነትና ህልውና ላይ በወታደራዊ ጉልበቱና በእጅ ባስገበው ከፍተኛ የሃገር ሃብትና ሌሎችም ግብአቶች የተነሳ ተጨባጭ የጥፋት እርምጃ እየወሰደ ካለው የወያኔ አገዛዝ ጋር በእኩልነት ልንመድባቸው የማንችል መሆኑን የሚጠቁሙ ናቸው።

በዚህ ሰነድ የግንቦት ሰባት ንቅናቄ “ባላጋራዎችንና ደጋፊዎችን ከማስበርገግ ይልቅ የማቅረብን አስፈላጊነት” መሰረት አድርገን ሲል ከግንቦት ሰባት ንቅናቄ ጋር ከአንድነት ጥያቄ አንስቶ በተለያዩ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ አንድ አይነት አመለካከት የሌላቸው ነገር ግን ወያኔን የሚቃወሙ የፖለቲካ ሃይሎች እንዳሉ ኣውቆ ነው። በሃገራችን ፖለቲካ ትንሽም ይሁን ትልቅ ልዩነት ካለን ቡድኖች ጋር በተለምዶ ለፍረጃ ከምንጠቀምበት ጠላት ከሚል ቃል ይልቅ ከግንቦት 7 ጋር መሰረታዊ የሆኑ ልዩነቶች ያላቸውን ሃይሎች ንቅናቄያችን ባላጋራዎች በሚል ቃል ለመግለጽ የፈለግነው ከጠላት ይልቅ ከባላጋራ ጋር የሚኖርን ልዩነት በውይይት በድርድር በሽምግልና ተቀራርቦ በመስራት መፍታት ይቻላል የሚል እምነት ስላለው ነው። ዛሬ ሁላችንም ባለንበት በወያኔ በተመረተ አጠቃላይ የውርደትና የግፍ ማጥ ውስጥ ተቀምጠን የትኛውንም ጸረ ወያኔ ሃይል ልዩነታችንም ትልቅ የሆኑትን አካላት ሳይቀር በጠላትነት መፈረጅ ለወያኔ ካልሆነ ለማናችንም የሚበጅ እንዳልሆነ ስላመንንበት ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ሁሉንም ባላጋራና ደጋፊ አድርገን እንድናይ ያስገደደን ዛሬ በሃገራችን የሃይል አሰላለፍ ከወያኔ በላይ ለሃገርና ለህዝብ አንድነት የከፋ ጠላት የለም የሚለው ተጨባጭ የእውነታ ግንዛቤ ነው። ይህ አይነቱ አካሄድ መሰረታዊ የቅራኔ አፈታት ህግ የሚጠይቀው አካሄድ ነው። ወደፊት በሂደት እንደሁኔታው ሊፈቱ የሚችሉ ቅራኔዎችን በአንደኛ ደረጃ አምጥተን ወቅቱንና የጸረ ወያኔን ካምፕ አቅም

ግምት ውስጥ ያላስገባ የወዳጅና የጠላት አፈራረጅ የሃገር አንድነትንም ሆነ የዜጎች አንድነት ለማስጠበቅ እንዲሁም ብዙዎቻችን የተሸከምነውን የህዝብ ሙብት የማስከበር ህልማችን እንዳይሳካ የሚያደርግ አካሄድ ነው ብለን ስለማናምን ነው። መሬት የያዘ የፖለቲካ ስራ በስሌትና በስልት እንጂ በስሜትና በፍላጎት ላይ የሚፈጸም አለመሆኑን በመገንዘብ ነው። ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት፣ ወታደራዊ ጡንቻው የፈረጠመ፤ መጠን የሌለው ሃብት ዘረፎ በእጁ ያስገባ፤ ራሱን በቅጥረኛነት በማቅረብ የኢትዮጵያን ህዝብ አፍኖ ሃገራዊ ድህነትና ጥቅሚን እንዳሻው እየሸቀጠ ያለ፤ በስልጣን ለመቆየት ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ፣ የወታደራዊና የስለላ ድጋፍ ከምእራብና ከምስራቅ ሃያል ሃገሮች እያገኘ ያለን አገዛዝ ታግለን ማሸነፍ የምንችለው ትግሉ የሚጠይቀውን ያሚላ መሬት ላይ የቆመ ስሌት ሲኖረን ነው።

ይህ ስሌት የወያኔን ጥንካሬ ከራሳችን ጥንካሬ ጋር ማነጻጸር ይኖርበታል። ይህ ስሌት የሚያሳየው ጸረ ወያኔ ድርጅቶች እንኳንስ በተናጠል ሄደውበት ይቅርና በጋራም እንኳን ተሰባስበው ዛሬ ባሉበት ደረጃ የወያኔን የተደራጀና የፈረጠመ አገዛዝ ለማግደርደር ምን ያህል ከባድ ስራ እንደሆነ ከግንዛቤ ያስገባ ነው። ይህ እውነታ የጸረ-ወያኔ ካምፑ እርስ በእርሱ በጠላትነት የሚፈራረጅበት ሳይሆን ከሚለያዩት ነገሮች ይልቅ በሚያስማሙት ነገሮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ በጋራና በህብረት ለመታገል ማንኛውንም ጥረት ማድረግ የሚገባው መሆኑን የሚያሳይ ነው።

**ግንቦት 7ትም ሆነ ጥምረታችን ከወያኔ ውጭ ያለውን ጸረ-ወያኔ የሆነ ሃይል ባላጋራና ወዳጅ በማለት የፈረጀው፤ ልዩነት የለንም ብሎ በማሰብ ሳይሆን ባላንጣ ወይም ጠላት የሚለውን ቃል ከወያኔ ውጭ ለሚገኝ ማንኛውም ጸረ-ወያኔ የፖለቲካ ድርጅት መጠቀም በተጨባጭ ወያኔን እንጂ የህዝብ ወገኖችን ፍላጎት በማስፈጸም አንድ ጋት የማያነቃንቅን እንደሆነ ስላመንበት ነው።** ከዚህም መሬት ላይ ከተከለ የሃይል ሚዛንን ግምት ውስጥ ማስገባት ካለበት የፖለቲካ ስሌት በተጨማሪም ግንቦት 7 ንቅናቄ ለወሰደው አቋም ሌላም ተጨማሪ ምክንያት አለ። በሃገራችን ያለው እውነታ በተለይ ወያኔ ባለፉት 20 አመታት በመላው የሀገሪቱ ዜጎችና ማህበረሰቦች ላይ የፈጸመው ግፍ፣ አዋራጅ ድርጊት፣ ዘረፋና ገፈፋ በማህበራሰባችን ውስጥ በመከፋፈል ላይ የተመሰረተ ፖለቲካን አደገኛነት ያስተማረ ሆኗል የሚል እምነት አለን። በግለሰብ ደረጃ የግሌን ብቻ ብሎ በመሮጥ፣ በማህበረሰብ ደረጃ ደግሞ የዘውግ የማህበረሰቤን ብቻ ብሎ በመሮጥ የሚገኝ ትርፍ እንደሌለ የተቀሰመው ትምህርት ከዜጎች አልፎ በልዩነት ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ አደረጃጀት ላይ በቆሙ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎችም ላይ ተጽእኖ እያደረገ ነው። ይህን አዎንታዊ ሂደት ማስቆም አይቻልም የሚል እምነት ይዘን ስለነበር ነው።

ዛሬ በሃገር ውስጥ የሚገኙ በተናጠልና በቡድን በከፍተኛ ደረጃ ወያኔ ያዋረዳቸው ህጋዊ የተቃዋሚ ድርጅቶች፣ በአንድነት በጋራ ተባብሮ ለመስራትና ትብብራቸውንም ወያኔን ለመጣል ብቻ ሳይሆን፣

ከወያኔ ውድቀት በኋላ የሚመጣውን የጋራ ፈተና በጋር ለመሸከም አቅደው የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ ፈጥሯል። ደግመው ደጋግመው በመግለጫቸው ሲሉት የምንሰማው "ከመነጣጠል ውድቀታችን ብዙ ተምረናል። የረባና ዘላቂ ትብብር መፍጠር ካለመቻል ውድቀታችን ብዙ ተምረናል። ሰዎች ነንና ከስህተት እንማራለን ተባብሮ ለመስራት ለያዝነው ህልም ድጋፋችሁ አይለን። እንዳለፉት ትብብሮች ይህኛውም ትብብር አይሰራም በሚል ምጸት አትመልከቱን" እያሉ ነው።

በሌላ በኩልም በልዩነት ላይ ድርጅታቸውን ያዋቀሩ ከወያኔ ህጋዊ ፈቃድ ውጭ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶችም በልዩነት ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ እምነትና አደረጃጀት ፍሬ ማፍራት ያልቻለ፤ የመከነ መሆኑን የተረዱበት በውስጣቸውም የድርጅቶቻቸውን ነፍስ መፈተሽ የተገደዱበት ሁኔታ ውስጥ እንዲገቡ ያደረጋቸው መሆኑን በቂ መረጃዎች አሉን። በኦሮሞ ልሂቃንና የፖለቲካ ሰዎች መሃከል የሚካሄደው ክርክርና ውዝግብ ኣንዱ ምክንያት የኦሮሞን ህዝብ ስቃይ፣ ውርደትና እንግልት ማስቆሚያው መንገድ የተናጠል ፖለቲካ ማራመድ ወይስ ፖለቲካችንን በተመሳሳይ ውርደት እንግልትና ስቃይ ውስጥ ከወደቀው ወገናችን ጋር በማቀናጀት ለሁላችንም የሚበጅ ሃገራዊ ሁኔታ እንዲፈጠር ወሳኝ ሚና እንጫወት በሚለው ጉዳይ ላይ ያጠነጠነ ነው። ይህ ሃቅ የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ገና ከመጀመሪያው ጸረ-ወያኔ የሆነውን የትኛውንም አካል በልዩነት ላይ የተመሰረተ አጋር እንጂ ጠላት ብለን መፈረጅ የለብንም ብለን የወሰድነውን አቋም ትክክለኛነት የበለጠ የሚያጠናክር ነው። ይህ ሃቅ ከወያኔ ሌላ በጠላትነት ልንፈርጀው የሚገባ ሃይል ሊኖር አይገባም በማለት የወሰድነውን አቋም ትክለኛነት የሚያረጋግጥ ነው።

ከዚህ በላይ ያልኩት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከቀሪው የንቅናቄው አቋም መረዳት እንደምችሉት፣ የግንቦትን ንቅናቄ ሁሉንም ጸረ ወያኔ ሃይል በጠላትነት ሳይመለከት፣ ከሁሉም ጋር በአንድነትና በህብረት ወያኔን ለማስወገድ መስራት ይቻላል የሚል እምነቱን ይዞ ሲንቀሳቀስ፤ ይህ አቋሙ ትርጉም እንዲኖረው ከተፈለገ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ካሉ እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች እንዲሟሉ ፊት ለፊት ከመጠየቅ የታቀበባቸው ጊዜዓት የሉም። እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች በሚያስረሳ ጭፍን የጸረ ወያኔ ጥላቻ አልተነዳም። የጸረ ወያኔ ጎራ አቅም በማጎልበትና የትግል ቅልጥፍና በመጨመር በጋራ መግባባት ልንደርስባቸው የሚገቡ ወሳኝ ጉዳዮችን ማንንም ግራ በማያጋባ ቋንቋ አስቀምጧል። ከነዚህ ጉዳዮች ለትብብራችን መሳካት የጋራ መግባባት ልንደርስባቸው ከሚገቡን ጉዳዮች መሃል ዋንኛው **ኢትዮጵያን እንደ ኣንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ መቀበል** ወይንም የኢትዮጵያን አንድነት በሚመለከት መሆኑን ግልጽ አድርገናል።ይህንንም አቋማችንን:

**"የኢትዮጵያ ሉዐላዊ አንድነትን ከተቀበሉና ከሚቀበሉ፣በሃገራችን የፖለቲካ ጉዳይ ያገባናል ብለው ከሚንቀሳቀሱ ከማናቸውም ፓርቲዎች ጋር በህብረት በመታገል"**

በሚለው አባባላችን ገልጸነዋል። ይህን ነጥብ በድርጅታችንና በአባላት መተዳደሪያ ድንብ ስናስቀምጥ ይህ ጉዳይ በዚህ መንገድ ግልጽና በማያሻማ ቋንቋ መቀመጡን የማይወዱ የፖለቲካ ድርጅቶች እንደሚኖሩ አጥተነው አልነበረም። ጸረ ወያኔ ትግሉ ያለበትን ዝቅተኛ የድርጅት አቅም፣ የሃገራችን ህዝብ በጋራ በጸረ ወያኔ ትግሉ ላይ ሊነሳ የሚችለው፤ ወያኔ በአለም አቀፍ ደረጃ ያለውን "የአካባቢው ብቸኛ የሰላምና መረጋጋት ሃይል" ነው በሚል ያገኘውን ጊዜያዊ ተቀባይነትና ከዚህ ተቀባይነቱ ጋር በተያያዘ የሚያገኘውን አለም አቀፍ ድጋፍ ማክሰም የምንችለው፣ ከዛም አልፈን ህዝብ ከፍተኛ መስዋእትነት ከፍሎ የሚቀዳጀውን ድል መልሶ በሌላ አምባገነንና ዘራፊ እንዳይቀማ ለማድረግ የምንችለው፣ ሁላችንም ጸረ ወያኔ ትግላችንና ከወያኔ ውድቀት በኋላ በሃገራችን ሆነ በከባቢያችን እንዲፈጠር የምንፈልገውን ሁኔታ "ኢትዮጵያ" በምንላት ሃገራችን ውስጥ ተሰባስበን የምናከናውነው መሆኑን በግልጽና በማያሻማ ቋንቋ በአደባባይ የሚታይ አቋም አድርገን ስናስቀምጠው ብቻ ነው ብለን ስላመንን ነው። ይህእምነት ብቻ ሳይሆን ከጀርባው የሁሉንም ዜጎች ብሄር፣ ብሄረሰቦች፣ ደቂቅና ሊቅ ስሜትና ፍላጎት ያካተተ ከዚህ ውጭ ከጋራ ባርነት ከውርደት ከስደትና ከድህነት መገላገያ መንገድ ሊኖር አይችልም ብለን ስላመንንበት ነው።

በሃገር አንድነት ላይ የወሰድነው አቋም፣ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ የተወሰደ አይደለም። ይህን አጀንዳ በማንሳት ራሳችንን ከሌሎች በመለየትና መስመር በማስመር የድርጅት አባልና ተባባሪ ማፍራት፤ ድጋፍ ማሰባሰብ ይቻላል ከሚል የፖለቲካ አቋምን ደንበኛ እንደሚያሰባስብ ነጋዴ በሸቀጥነት ተመልክተን አይደለም። ይህ አቋም ለማስመሰልና ለመግደርደር (posturing) ለእይታ የቀረበ አቋም አይደለም። የሃገራችንን ህዝብ ስቃይና መከራ ማሳጠር የወደፊቱን እጣ ማሳመር የሚቻለው በሃገር አንድነት ጉዳይ ላይ ሁላችንም ግልጽ የሆነ አቋም ይዘን ትግላችንን ስናስተባብር ብቻ ነው የሚል ጽኑ እምነት ስላለን ነው። ምንም ያህል አድካሚና አስቸጋሪ ቢሆን በጸረ-ወያኔ ካምፕ ከሚገኙ በአንድነት ጉዳይ ላይ ተመሳሳይ አመለካከት ከሌላቸው ሃይሎች ጋር መወያየት መምከር በሃገር አንድነት ላይ የጠራ አቋም ይዘው በጋር እንድንሰራ ጥረት ማድረግ አለብን የምንለው እነዚህ ሃይሎችም ሆኑ ሌሎቻችን በዚህ መንገድ ከሚመጣ ትብብር ውጭ የማናችንንም መከራና አሳር ማስቀም የማንችል እንደሆነ ከልባችን ስላመንበት ነው። በዚህ እምነት ላይ የቆመው የሃገራችን ህዝብ ግፊት እየተከማቸና ግፊቱን መሸከም ከማንችልበት ደረጃ ላይ እያደረሰን ነው የሚል እምነት ስላለን ነው።

የግንቦት 7ና የጥምረቱን አመራርና አባላቱን የሚገዛው የሃገር አንድነትና የትብብር አቋም ከዚህ በላይ የገለጽኩት ነው። ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር የምናደርገውን ግንኙነት የሚወስነው ይህ የድርጅቱ ፖሊሲ ነው። ይህን ያዳመጠና ያነበበ ማንም ቀና ሰው በድርጅታችን የአንድነት እይታ ላይ ምንም ብዥታ ሊኖረው አይችልም። በአንድነት ጥያቄ ላይ የወሰድነው አቋም፣ እንዲሁም አንድነትን ከእኩልነት፣

የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብቶች ማስከበርን፤ ማእከሉ ያደረገ የትብብር ጥሪያችን፤ ተጨንቀን ተጠበን ብዙ ጉዳዮችን መርምረን ግራ ቀኙን አገላብጠን የወሰድነው አቋም እንጂ ሁኔታዎችን ሳንመረምር ለሃገራችን ካለን ፍቅር ብቻ ተነስተን በስሜት የወስድነው አቋም እንዳልሆነ ለማየት እንድትችሉ ያደረግሁ ይመስለኛል። ይህን ካልኩ ቀጥዬ የምሄደው ወደ ንግግሬ ሁለተኛ ክፍል ይሆናል።

## 2. ልዩነት በሌለበት ልዩነትን መፈለግ - በአንድነትና በዴሞክራሲ ጥያቄ ዙሪያ

ቀደም ብየ እንደጠቀስኩት ከፊዚክስና ከማቲማቲክስ እየወጣን ወደ ማህበራዊ፣ ፓለቲካዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ሰነ-ኪነት፣ ስነ-ሞራል፣ ታሪክንና ተመሳሳይ ወደ ሆኑ የእውቀት ዘርፎች ስንመጣ እውነትና ሃቅ የሚመዘኑባቸው መስፈረቶች የጋራ ተቀባይነታቸው እየጠፋ፣ እውነት ከያንዳንዳችን የግልና የቡድን ስሜት ፍላጎትና ዝንባሌ ውጭ በራሱ የቆመ ነገር መሆኑ እያበቃለት ይሄዳል። በተፈጥሮ ሳይንስም ቢሆን ፍጹም እውነት የሚባሉ ነገሮችም እየተመናመኑ መሆናቸውን እያየን ነው። የእያንዳንዳችን ዝንባሌ፣ ስሜትና ፍላጎት ከላይ በጠቀስኳቸው የእውቀት ዘርፎች ዙሪያ እውነትና ሃቅ ብለን በምናቀረበው ጉዳይ ላይ ታላቅ ተጽእኖ እንደሚያደርግ ግልጽ ነው።

ወያኔን በሚቃወሙ የፖለቲካ ሃይሎች መሃል በብዙ ጉዳዮች ላይ ያለውን ተመሳሳይ የሆነ አመለካከት ማየት እንዳንችል ያደረገን ጉዳይ ሁላችንም፣ የአንድነት ታሪክንና ፖለቲካን በሚመለከት በየግላችን ወይም በቡድናችን የያዝነው እውነት እንደ ማቲማቲክስና ፊዚክስ እውነቶች፣ አንዳንዴም ከነዚህ የእውቀት ዘርፎች ውስጥ ከሚገኝ እውነትና ሃቅም በላይ "ንጹህ፣ የተጣራ ሃቅ፣ እውነት" ነው ከሚል በምንም በአመክኖ ሊደገፍ ከማይችል ግትርና የተሳሳተ አቋማችን የሚመነጭ ነው። የአንድ ጭብጥ እውነተኛ ገጽታ በሁለት ተቃራኒ ጫፍ ግትር አቋሞች ከያዙ ሁለት አካላት እጅ ባንዱ ወገን ብቻ የተያዘ እንደሆነ አድርጎ ማየት ለችግራችን ስር መስደድ ምክንያት ሆኗል። ይህ የተሳሳተ እይታ ምን ያህል ጉዳት እያደረሰ እንደሆነና ይህ እይታ በሌሉና ሊኖሩ በማይችሉ ልዩነቶች ላይ እንድናተኩር በማድረግ፣ አብዛኛዎቹ ልዩነት ብለን የያዝናቸው ጉዳዮች ዛሬ በጋራ ሁላችንም የገጠመንን እዳና ፍዳ ከማቃለል ስራ ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌላቸው ለመረዳት እንዳንችል በማድረግ የሁሉንም የሃገራችንን ህዝብ ስቃይ እያራዘሙ ይገኛሉ የሚል ጽኑ እምነት አለኝ። ይህንን እምነቴን እንድትጋሩልኝ ለማድረግ ለአንድነት ቆመናል በሚሉ ሃይሎችና ልዩነትን ማእከል አድርገው በሚንቀሳቀሱ ሃይሎች መሃል በዋንኛነት አጨቃጫቂ ሆነው በተለምዶ የምናያቸውን ጉዳዮች በምሳሌነት ተራ በተራ እያነሳሁ ለማሳየት እሞክራለሁ። በዚህ ሙከራዬ እነዚህን ጉዳዮች ተራ በተራ ስንመለከታቸው በምን እንደምንለያይ ሁላችንም ግራ እስከሚገባን ድረስ የሚያስገርመን ጉድ ማየት እንችላለን ብዬ አምናለሁ።

በቅድሚያ ቀደም ብዬ በጠቀስኩትና በሃገራዊ አንድነት ጉዳይ ዙሪያ ለሚነሱ ውዝግቦች ምንጭ ነው ባልኩት፣ ኢትዮጵያ ከዘመናዊ ሃገርና መንግስት ምስረታ ጋር ያለፈችበትን ሂደት በተመለከተው ጉዳይ ልጀምር። በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ምን እንደሚያስማማንና እንደሚለያየን በቀላሉ ለማየት እንዲረዳን ጥያቄዎችን በማቅረብ ይህን ንግግር የሚያዳምጡትም ሆነ በጽሁፍ የሚያነቡት ወገኖቼ ለማነሳቸው ጥያቄዎች በህሊናቸው መልስ በመስጠቱ እንዲተባበሩኝ የሚጋብዝ ይሆናል።

ጥያቄዎቼንና መልሶቼን ልደርድር።

1. በአብዛኛው የአለማችን ክፍሎች ያሉ አብዛኛዎቹ ዘመናዊ ቅርጽ የያዙት ሃገሮች በእሳትና በብረት፤ በወረራና በማስገበር እርምጃ የተፈጠሩ እንደሆነ የማይስማማ አለ? ለምሳሌ ያክል እንኳን እዚህ ያለንባት ዘመናዊቷ አሜሪካ በኔቲቭ አሜሪካኖች ደምና ስርነቀል መፈናቀል የተፈጠረች፤ የአሜሪካንን ዴሞክራሲ የፈጠሩት እነ ጆርጅ ዋሽንግተን የባርያ ባለቤቶች መሆናቸውን እናውቅ የለም?

2. በኢትዮጵያ የዘመናዊ ሃገርና መንግስት ግንባታ በእሳትና በብረት፤ በወረራና በማስገበር የተከናወነ መሆኑን እዚህ ውስጥ የሚክድ ሰው አለ? እኔ ያለ አይመስለኝም።

3. በዚህ በሀገራችን ዘመናዊ ሃገርና መንግስት ምስረታ ጋር በተያያዙ መስፋፋቶችና ወረራዎች ማህበረሰቦች የወደሙበት፤ የተዘረፉበት፤ እልቂት የተፈጸመበት፤ ባህላቸውና ቋንቋቸው የተረገጠበት ሁኔታ ውስጥ እንዲገቡ እንደተገደዱ የሚክድ አለ? እንዲህ አይነቱን ግፍ ሰዎች በአመጽ ከመሸነፍ ውጭ ወደው ይቀበሉታል ብሎ የሚያምን አለ?

4. የዘመናዊ ሃገርና መንግስት መስራች ተብለው የሚታወቁት አጼ ምኒሊክ ዘመናዊ ሃገርና መንግስት ሲመሰርቱ ዛሬ በሃገሪቱ የተሰባሰቡትን ከ80 በላይ የሚቆጠሩ ብሄር ብሄረሰብ ተወላጆች ፈቃደኛነት ሬፈረንደም እየጠየቁ ድምጽ እያሰጡ ማከናወን ይችሉ ነበር? ያኔ ሪፈረንደም ማሰጠት ነበረባቸው ብሎ የሚሟገት አለ?

5. በዚያ ወሳኝ የሆነ የታሪክ ወቅት በምኒልክ ምትክ የአጼ ዮሃንስ ልጅ ራስ አርአያ ወይም የሸዋው ኦሮሞ  የጦር አበጋዝ ራስ ጎበና ወይም የጅማው አባጅፋር ወይም የወላይታው ንጉስ ጦና የአካባቢው ብቸኛው ጉልበተኛ  ሆነው ቢሆን ኖሮ ከእነዚህ አንዳቸው የድምጽ መስጫ ሳጥን እያስቀመጡ "ልመሰርተው የምፈልገው ዘመናዊ ሃገርና መንግስት አካል መሆን ትፈልጋላችሁ?" የሚል የምርጫ እድል በሃገሪቱ ውስጥ ለሚገኙ ዘውጌ ማህበረሰቦች ይሰጡ ነበር? በዚህ "ላስገብርህ_አታስገብረኝም" የረጅም ጊዜ ትግል ሁሌም አሸናፊው አንድ ወገን ብቻ ነበር? በየጊዜው የአሸናፊው ሀይል ሌላውን አንዴም እየረገጠ፤ ሌላ ጊዜ እያባበለ፤ የተሸናፊውን ወገን የሱ ፖለቲካ ማህበረሰብ አካል አላደረገም?

6. እስካሁኑ ዘመን የዘለቀው ችግራችን የሃገራችንን ዘመናዊ መንግስትና ሃገር ምስረታ በከፍተኛ አመጽና እልቂት መገንባቱ ሳይሆን በዚሁ አይነት መንገድ ዘመናዊ መንግስትና ሃገር እንደ መሰረቱ የአውሮፓ ሃገሮች፣ እልቂቱን ጦርነቱን ገባሪነቱን ሊያስረሳ በሚያስችል ሁሉንም ህዝብ በእኩል ተጠቃሚ ማድረግ በሚችል የኢኮኖሚ እድገት፤ የማህበራዊ አገልግሎት መስፋፋትና የሁሉንም ሙብት ማስከበር በሚችል የፖለቲካ ስርአት በሀገሪቱ ላይ መትከል ካለመቻላችን ጋር የተሳሰረ ጉዳይ እንደሆነ የሚክድ ሰው አለ?

7. ይህን ማድረግ ተችሎ ቢሆን ኖሮ ዛሬ የሃገራችን ፖለቲካ በዘመናዊ ሃገርና መንግስት ምስረታ ወቅት በተከሰቱ የመገበርና የማስገበር የጦርነትና የእልቂት ታሪክ ዙሪያ ከመጠመድ ወጥቶ ትኩረቱ እንደኛው ዘመናዊ ሃገርና መንግስታቸውን በአመጽ እንደመሰረቱ ሃገሮች ከታሪክ ውጭ በሆኑ የኢኮኖሚና  የማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ይሆን እንደነበር የሚጠራጠር አለ?

8. እንዲያው ደፈር እንበልና ኢትዮጵያ ዘመናዊ ሃገርና መንግስት የመገንባቷን ሂደት በጀመረችበት የታሪክ ምእራፍ በሃገሪቱ ውስጥ የነበረው የዘመናዊ እውቀትና ቁሳዊ ክምችት ለምሳሌ በአመራረትና በአኗኗር በአስተዳደር በወታደራዊ አደረጃጃት እንዲሁም በሌሎች ዘርፎች ምን ይመስል ነበር? ፈጣንና ዘመናዊ የአስተዳደርና የአመራረት ለውጦች ማከናወን የሚያስችል ነበር?

9. ከዚህ ላይ በዘመናዊ ስልጣኔ የተራመዱ ከፍተኛ  ሃብትና የወታደራዊ ጉልበት ያላቸው ሃይሎች አፍሪካን በቅኝ ግዛትነት ተቀራምተው ኢትዮጵያንም የቅኝ ግዛታቸው አካል ለማድረግ ደጃፏ በደረሱበት ወቅትና ይህንን የቅኝ ግዛት ወረራ ለመከላከል የሃገሪቱ ህዝቦች ጉልበትና አነስተኛ ሃብት መጥፋት በጀመረበት፣ ሃገሪቱ በውስጣዊ አስተዳደሯ እርጋታና ሰላም አግኝታ ፈቷን

ወደልማት ማዞር ባልቻለችበት ሁኔታ፣ የሃገራችን ዘመናዊ ሃገርና መንግስት ግንባታ ሂደት በአውሮፓ እንደታየው በሁሉም ዘርፍ በተገለጸ ፈጣን የዘመናዊነት እድገት ሊታገዝ ይችል ነበር ወይ?

10. ፈጣንና ዘመናዊ እድገት ለማምጣት የማያስችል የሀገራችን የእውቀትና የግብአት ማነስ በአንድ በኩል፣ በሌላ በኩል ደግሞ በተከታታይ ሃገሪቱ የገጠማትን ራሷን ከውጭ ወራሪዎች የመከላከል ፈተና ግምት ውስጥ አስገብተን፣ታሪክን ከስሜታዊነት ነጻ በሆነ መንገድ ስንመለከተው በአጼ ምኒሊክ መሪነት የተጀመረውና አጼ ሃይለ ስላሴ የተረከቡት ዘመናዊ ሃገርና መንግስት የመገንባታ ሂደት የግዛት አንድነትን ከማስጠበቅና ግዛትን ከውጭ ወራሪዎች ከመከላከል አልፎ በሌሎች ሃገሮች የታየውን ፈጣንና ስር ነቀል የስልጣኔ ግስጋሴ ማምጣት ይችል ነበር ብለን ማሰብ እንችላለን?

11. ከዚህ በላይ የጠቃቀስኳቸው የታሪክ ጭብጦች እውነት መሆኑን ተረድታችሁ ስታበቁ፣ እንዲህ አይነቱን የስልጣኔ ግስጋሴ ማምጣት በማይችሉ ነገስታት እጅ ከምንወድቅ በስልጣኔ በገሰገሱት የአውሮፓ ነጭ ቅኝ ገዥዎች እጅ ሁላችንም በጋራም ይሁን በተናጠል ብንወድቅ ይሻል ነበር የምትሉ ስንቶች ናችሁ?

ይህን የማነሳው ያለምክንያት አይደለም። በዛ የታሪክ ወቅት የሀገራችን ህዝቦች የነበራቸው አማራጭ አንድም አካባቢ በቀል በሆኑ ሃይለኞች መገዛት አሊያም በቅኝ ገዥዎች እጅ መውደቅ ብቻ ነበር ብዬ ስለማስብ ነው።

12. ለመሆኑ በዚያ ወቅት ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ ብሄርብሄረሰቦች መሃል በቅኝ ገዠዎች እጅ ሳይወድቅ እንዲሁም ለአካባቢው ሃይለኛ ሳይገብር ለብቻው እራሱን በራሱ ተከላክሎ እንደማህበረሰብ ራሱን ጠብቆ ይዘልቅ የነበረ ሃያል ማህበረሰብ ነበርን? ከነበረ ያ ማህበረሰብ ማን እንደሆነ ምሳሌ ሊሰጠኝ የሚችል አለ?

13. የኢትዮጵያ ህዝብ እጅግ አስከፊና አሰቃቂ ሃገራዊ የአገዛዝ ሁኔታዎች ውስጥ በአመጽ ሃይል እንዲሰባሰብ ተደርጎም ቢሆን በዚህ መሰባሰብ በተገኘው የሰውና የቁስ ግብአቶች በጋራ ከየአቅጣቻው የመጡበትን ወራሪዎች መመከት ባይችል ኖሮ በሰሜን እንደታየው ጣልያን፣

በምእራብና በደቡብ እንግሊዝ፣ በምስራቅ ፈረንሳይ እንግሊዝና ጣልያን ቡጭቅጭቃችን የማውጣት አቅም ያገኙ እንደነበር የሚጠራጠር አለ?

14. በዚህ መንገድ ቅኝ ገዥዎች ተቀራምተውን ቢሆን ኖሮ ባህላችን ቋንቋችን እምነታችን እንዲያው ባጠቃላይ ማንነታችን (identity) ይተርፍ ነበር ወይ? ቅኝ ገዦዎቹ ቢይዙን ኖሮ "ቋንቋችንን እንድናሳግ፤ ባህላችንን እንድናበለጽግ፤ የአካባቢያችን ሃብት ተጠቃሚዎች እንድንሆን፤ ለየአንዳንዱ ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ ብሄር ብሄረሰቦች ሁኔታውን ያመቻቹ ነበር" የሚል እምነት ያለው ሰው አለ?

15. የዘመናዊ የሃገርና የመንግስት ግንባታ የወረራንና የማስገበርን የደምና የእምባ ቅርሱን ሳይጠርግ፣ በባርነት፣ በጭሰኝነትና በገባርነት ላይ ከተመሰረተ ኢፍትሃዊ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ግንኙነት ሳይላቀቅ፤ መብት ገፈፉን ብዝበዛን ሰብአዊ ውርደትን ከስርአቱ መገለጫዎችነት ሳያጠፉ በታሪክ ቅጥልጥሎሽ ከትውልድ ትውልድ ለረጅም ዘመን መዝለቁ ዛሬ ላለንበት ምስቅልቅል ዋናው ምክንያት እንደሆነ የሚክድ አለ? እኔ ያለ አይመስለኝም።

16. ይህ ከመራቆትና ከመታረዝ ከመዋረድና ከሙብት መገፈፍ ጋር የተያያዘ የታሪክ ቅጥልጥሎሽ መልኩን እየቀያየረ እስካለንበት ዘመን መዝለቁን የሚክድ አለ? ዜጎችና ማህበረሰቦች ዛሬም ቢሆን በግልም ይሁን በቡድን ስለሚደርስባቸው ውርደትና ብዝበዛ ሲያሰላስሉ ይህ ውርደትና ብዝበዛ የታሪክ ቅጥልጥሎሽ ያለው፣ የዛሬ በደል ከትናንቱ በደል ጋር የተያያዘና ተመሳሳይነት ያለው መሆኑን አጥብቀው ቢናገሩ ለምን ወደኋላ ይመለሳሉ የሚል ጥያቄ አንስተን መደናበር ይገባናልን?

ይህንን በሌላ መንገድ ላቅርበው።

አንዲት እህታችን ተነስታ

"አዎን ሁሉም ሃገሮች ዘመናዊ ሃገርና መንግስት ምስረታቸውን ያካሄዱት በእሳትና በብረት ሃይል እንደሆነ አውቃለሁ። የኛም ሁኔታ ከዚህ የተለየ ሊሆን እንደማይችል ይገባኛል። የኛጉዳይ ግን ከሌሎች ለየት የሚያደርጉት ነገሮች አሉ። እልቂቱ መጋዙ መገበሩ ከብዙ መቶዎች አመታት በፊት የሆነ በታሪክ ብቻ የሚታወስ ጉዳይ አይደለም። የባሪያነቱና የጢሰኝነቱ ጠባሳ ከአያንዳንዶቻችን ጀርባ ላይ ገና ያልጠፉ፣ በማስገበር ጦርነት እሳት የጋዩት የቅድመ አያቶቻችንና ሴት ወንድ ልጆች የእልቂት ዋይታ

አሁንም በጆሯችን የሚቃጭልብን፣ እስካሁንም ይህን የታሪክ መጥፎ ውርስ እንዲሸር የሚያደረግ ሳይሆን የበለጠ እንዲሰማን የሚያደርግ ግፍ እየተፈጸሙብን ያለን ወንድሞቻችሁና እህቶቻችሁ አለን። ክርክራችን ታሪክ ለምን ራሱ መፍሰስ ከሚችልበት ቦይ ውጭ አልፈሰሰም የሚል አይደለም። ቁጭታችን ምሬታችን ጥላቻችን የሚያቀጣጥሉት እውነታዎች ሞተው የተቀበሩ አይደሉም።ይህን ልትረዱልን ይገባል" ብትለን የሚሰማ ጆሮና የሚያዳምጥ ልብ ለመስጠት ስህተቱ ምን ላይ ይሆናል? "ሁላችንም ተበድለናል ያንቺ በደል ከኛ በደል የከፋ አይደለም"፣ እስቲ በደላችንን ሚዛን ላይ እናስቀምጠውና እንለካው የሚል የበደል ክብደት በማወዳደር ታፍና እንድትቀመጥ ማድረግ የሚጠቅመው ማንን ነው። ከዛም አልፎ አንዳንዶች እንደሚዳዳቸው "የምትይው ሁሉ ሃሰት ነው። ኢትዮጵያ በዜጎቿ ጉሮሮ ማርና ወተት የምታንቆረቁር፣ ሁሉንም በተባዘተ ጥጥ አቅፋ ስታኖር የነበረች ሃገር ናት" የሚል ክርክር ለመግጠም የሚያስችል የሃቅ መሰረት አለን?ይችን እህታችንን "የምትናገሪው ሁሉ የሃገራችንን ገጽታ ለማበላሸት፣ የውጭ ጠላት መሳሪያ በመሆን ወይም ሃሰትና ክፋት የማሰራጨት እኩይ ስብእና ስላለሽ ነው" የሚል መልስ መስጠት ተገቢ ነው የሚል አለ?

በሌላ መልኩስ የዘመኑ ትውልድ ቀደምቶቹ በሰሩት ሁሉ መጠየቅ አለበት የሚል አለ? ቀደምቶቻችንን ዛሬ በሰለጠነ ዘመን የምንኖረው ልጆቻቸው በተግባር ለማዋል ባቃተን፣ በነሱ ዘመን እጅግም በማይታወቁ፤ የዲሞክራሲ፣ የሰብአዊነት የመልካም አስተዳደር መስፈርቶች እየለካን የማውገዝ መብት አለን ብሎ የሚያምነው ስንቱ ነው? አያቶቻችን በገባሪነትና በአስገባሪነት ተቆራኝተው ኖረዋልና ዛሬ እኔና አንተ በእኩልነት ተከባብረን መኖር አንችልም፤ በአንድነት ተስማምተን ከምንኖር በድህነት በውርደት ተሳስረን ገሃነብ መውረድ አለብን የሚል እምነት ጤነኛ ነው? በቅድመ አያትህና በአያትህ ድርጊት አንተ ተጠያቂነህ የሚል አባባልና እይታ በዘመናዊ ፖለቲካ ውስጥ ቦታ ሊኖረው ይገባል የምትሉ ስንቶች ናችሁ?

ከዚህ በላይ ያነሳኋቸው ጥያቄዎችና ሁላችንም በቀና መንፈስ ለእነዚህ ጥያቄዎች የምንሰጠው ምላሽ በጥሞናና ረጋ ባለ መንፈስ መወያየት ስንጀምር በበርካታና መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ከልዩነታችን ይበልጥ የምንስማማባቸው ነጥቦች እንደሚበዙ ማየት የምንችል መሆኑን የሚጠቁሙ ናቸው። የማያስማሙን ነገሮች ቢኖሩም ወያኔ ከዘረጋው አምባገነናዊ ዘረኛ የአፓርታይድ ስርአትና በዚህ ስርአት ስር በሁላችንም ላይ እየደረሰ ካለው ውርደትና ስቃይ አንጻር ላለመስማማት ተስማምተን የምንሻገራቸው ጉዳዮች ሊሆኑ እንደሚገባ እንደምንስማማ ሙሉ እምነት አለኝ።

ከዚህ በላይ ካቀረብኳቸው ነጥቦች በተጨማሪ በተለያዩ በጸረ ወያኔ ካምፕ በተሰባሰቡ የተለያዩ የፖለቲካ ልሂቃን መሃል መቀራረብ ተፈጥሮ፣ በጋራና በአንድነት በምናደርገው ትግል ሁላችንም ከገባንበት ገሃነብ መውጣት እዳንችል የሚያደረጉ ለገለልተኛ ተመልካች እጅግ የሚገርሙ ጉዳዮችን አነሳለሁ። በቅድሚያ ግን ባሁኑ ዘመን በሃገራችን ከሚንቀሳቀሱ ቡድኖች መሃል ማንም ደፍሮ ፊት ለፊት ሊናገር በማይችላቸው ጉዳዮች ልጀምር።

በኢትዮጵያ የዜጎችና የቡድኖች መብት አልተከበረም። ዜጎች በነጻ የመናገር የመጻፍ የመደራጀት በነጻ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው ሰርተው መኖር የሚችሉበት መብት አልተከበረም። በኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ ብሄር ብሄረሰቦች አሉ። እነዚህ ብሄር ብሄረሰቦች በቋንቋቸው የመጠቀም ባህላቸውን የማሳደግ፣ ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር በአካባቢያቸው በሚገኝ ሃብት በዋንኛነት ተጠቃሚ የመሆን ፍላጎት አላቸው። ይህ ፍላጎት እውን እንዳይሆን ወያኔ የዘረጋው አፋኝ ዘረኛ አገዛዝ እንቅፋት ሆኗል። በኢትዮጵያ የህግ የበላይነት እና በህግ ፊት እኩልነት የሚባል ነገር የለም። የሚዲያ ነጻነት የለም። የህዝብ ሃብት ሲዘረፍ፤ የሀገርና የህዝብ ደህንነትና ጥቅም ሲቸበቸብ፤ ህዝብንና ሃገርን ግን ከጥቃትና ከበደል ሊከላከሉ የሚችሉ ህዝባዊና መንግስታዊ ነጻ ተቋማቶች የሉም። ኢትዮጵያ ድህነት በሽታ መሃይምነት ወዘተ ስር ሰደው የተንሰራፋበት የአብዛኛዎቹ ዜጎች የቀን ተቀን ህይወት በሲኦል መመሰል የሚቻልባት የስቃይ ሃገር ናት። የወያኔን አገዛዝ አስወግዶ በቦታው ዴሞክራሲያዊ ስርአት በመገንባት እነዚህን የሰብአዊና የሲቪል መብቶች እንዲከበሩ ማድረግ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ችግሮች መፍታት ጊዜ ልንሰጠው የማይገባ ተግባር ነው።

ከዚህ በላይ አጠቃልዬ ባቀረብኩ የሃገሪቱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እውነታና ችግሮች ላይ ልዩነት አለኝ የሚል የተቃዋሚ ሃይል አለ? አይመስለኝም። ለችግሮቹ መፍትሄ ይሆናል ብዬ ባቀረብኩ ጥቅል መፍትሄ ላይም ልዩነት የሚኖረን አይመስለኝም። ወያኔን የሚቃወሙ ሃገራዊና ክልላዊ የፖለቲካ ድርጅቶች በአደባባይ የሚሰጧቸው መግለጫዎች ከዚህ በላይ ካቀረብኩት ሃሳብ ሲጻረሩ አይተን አናውቅም። በሌላ በኩል ግን ይህን የሃገሪቱን እውነታ፤ ችግሮችና መፍትሄዎቹን የሚቀበሉና የማይቀበሉ ተቃዋሚ ሃይሎች ያሉ አስመስሎ በማቅረብ፤ በሌለ የአመለካካት ልዩነት ትልቅ ልዩነት እንዳለ አድርጎ ማቅረብ የተለመደ ነው። ይህ ደግሞ ስር የሰደደ ዛሬ ላለንበት አሳፋሪ ውርደት የዳረገን የቆየ የፖለቲካ ልሂቁ ባህል ነው። ዛሬም በኢትዮጵያ ውስጥ ሰዎች ጭሰኛነትን ሊመልሱ፣ ስልጣን በተለምዶ በማእከል ተከማችቶ የነበረበትን ሁኔታ መመለስ የሚፈልጉ፤ ስልጣን ወደ ህዝብ የሚቀርብበትን ያልተማከለ ፌደራላዊ አስተዳደራዊ ስርአት የሚቃወሙ፣ ብሄር ብሄረሰቦች

በቋንቋቸው መጠቀማቸውን ባህላቸውን ለማሳደግ የሚያደርጉትን ጥረት የማይደግፉ፣ ለኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ሳይሆን ፋሽታዊና አምባገነናዊ ስርአት ያስፈልጋል ብለው የሚያምኑ ሃይሎች የሚርመሰመሱበት ሁኔታ በሃገራችን እንዳሉ አድርጎ ማቅረብ የተለመደ ነው። እውነት እንነጋገር ከተባለ እነዚህ ሃይሎች የትነው ያሉት የሚል ጥያቄ ቢነሳ መልስ የሚሰጥ አይኖርም። ስልጣን ላይ ያሉትም አጭበርባሪ ዘረኛ አምባገነን ገዝዎች ሳይቀሩ በድርጊት ፋሽስታዊ ጫማዎቻቸውን እያነሱ ህዝባችንን ይርግጣሉ እንጂ አፋቸውን ሞልተው "ፋሽስታዊ ስርአትን ማንገስ ተገቢ ነው" ብለው ሲናገሩ አይደመጡም። እንዲህ አይነቱ አመለካከት ያላቸው ተቃዋሚ ድርጅቶች ቢኖሩ የትኞቹ ናቸው ብለን ብንጠይቅ መልስ የሚቸግረን ይመስለኛል።በተለይ ደግሞ እነዚህ ድርጅቶች ከየትኛው ማህበረሰብ የመጡ ምን ያህል ድጋፍስ አላቸው? የሚለው ጥያቄ ደግሞ የበለጠ ለመመለስ አስቸጋሪ ይሆናል።

በዚህ ስብሰባ ውስጥ "ዴሞክራሲ አያስፈልግም፤ የኢትዮጵያን ህዝብ በሙሉ በአንድ ቋንቋ ብቻ መናገር አለበት፤ የኢትዮጵያን ህዝብ በተማከለ ፋሽታዊ ጫማ እየረገጡ መግዛት ተገቢ ነው" የሚል ግለሰብ አለ?

ታዲያ ለምንድነው አንዱ ተቃዋሚ ሌላውን ተቃዋሚ በወጉ ሳያናግረው በመሃከላቸው ልዩነት እንዳለ አድርጎ የሚመለከተው? ይህ ማለት ዲምክራሲ እንዴት እንገንባ? ያልተማከለ አስተዳደር በምን መልክ ቢዋቀር የተሻለ ነው? ከድህነት መውጫው የተሻለው የኢኮኖሚ ፖሊሲ የትኛው ነው? በሚሉ ጉዳዮች ላይ ልዩነት አይኖርም ማለት አይደለም። መኖራቸውም ተገቢ ነው። **ችግሮች ለይቶ በማውጣትና በማወቅ መቶ በመቶ ስምምነት ላይ መድረስ የቻሉ ሃይሎች፣ እንዲሁም በጥቅሉ ቢሆንም ለችግሮቹ መፍትሄ ይሆናሉ ብለው በያዙት አቋም መቶ በመቶ ስምምነት ያላቸው ቡድኖች ወደመፍትሄዎቹ ዝርዝር ሲገቡ ልዩነታቸው መቶ በመቶ ይሆናል ብሎ ማሰብ የሚከብድ አይመስላችሁም።**

በቅርበትና ከስሜታዊነት ውጭ በመፍትሄዎቹም ዙሪያ ከምራችን ውይይት አድርገን ቢሆን ኖሮ ተመሳሳይነት ያለው አቋም እንዳለን ለማየት ከሌለንም ወደሚያቀራርቡን አቋሞች መድረስ አንችልም ነበርን? እኔ ያለጥርጥር ይቻላል የሚል ምላሽ እሰጣለሁ። እናንተስ?

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ለሃገር አንድነት በህዝብ አንድነት በጋራ ታግሎ  በጋር የጋራ ችግርን በመፍታት ጉዳይ ዙሪያ የምናደርገውን ጥረት የሚያወሳስቡ ማንኛውንም ቅን ተመልካች የሚያስገርሙ ለትዝብት የሚዳርጉንን ጉዳዮች አነሳለሁ። አሁንም ራሴንም እናተንም እየጠየቅሁ እቀጥላለሁ።

እስኪ አስቡት ...

> *ከ10ሽዎች አመታት በፊት ዛሬ ኢትዮጵያ የሚባል ሃገር ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ህዝቦች ኒሎቲክ  ነበሩ። ሴማውያኑ ትግሬውና አማራው ባህር አቋርጠው ከየመን አካባቢ የመጡ ናቸው። ከኩሾቹ ጥቂቶቹ እዛው የነበሩ ሲሆን ኦሮሞዎቹ ግን ከሴማውያኑም በኋላ ዘግይተው የዛሬ 800 አመት በፊት ከማዳጋስካር ተነስተው አፍሪካ ቀንድ የገቡ ህዝቦች ናቸው።*
> የሚል .....

ወይንም

> *ኒሎቲኮችንና ሴማውያኑን መጤዎች አድርጎ ኩሾቹ ብቻ የሃገሪቱ የጥንት ኗሪዎች አድርጎ የሚያቀርብ ክርክር ...*

**የዛሬ የመብት እጦታችንንና ድህነታችንን ለመቅረፍ አስተዋጽኦው ምንድነው?**

በአካባቢያችን ስለሚታዩ  የፖለቲካ ችግሮች እንነጋገር ብየ የጋበዝኩት የከምባታ ወንድሜ “ኤርትራ ውስጥ ጉርአ የሚባል ቦታ አለ ጉራጌዎች ከዛ ሳይሆን አይቀርም የመጣችሁት” በማለት የሚያነሳው ነጥብ ለምናደርገው ውይይት ፋይዳው ምንድነው? ከኔ ጋር መነጋገር አትችልም ወደመጣህበት ወደ ኤርትራ ሂድ ሊለኝ ነው? በዚህ አባባል የሚሳካለት ነገር ይኖራል? ችግራችን ይቃለላል? አይመስለኝም።

በእነዚህ ምእተ አመታት ትግሬዎች እዚህ ቦታ ነበሩ፤ አማሮችና ኦሮሞዎች እዛ ነበሩ እየተባለ በሙቶዎች አሙቶች ወደ ኋላ እየተመለስን ማን የት እንደነበረ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ  የወረደ የታሪክ

ማስረጃና ጸረ ማስረጃ የምናፈላልገው ወደፊት ነጻ የሆኑ ሃገሮች ስንመሰርት በግዛትና በድንብር ዙሪያ የሚነሳን ጭቅጭቅ በሰነድ ማሸነፍ ይቻላል ብለን ነውን?

እንኳን ወደ ኋላ በመቶዎች የሚቆጠሩ አመታት ቀርቶ ወያኔ በህገመንግስቱ ያስቀመጠውን የመገነጣጠል መብት በስራ ላይ እናውል ቢባል ዛሬ ወያኔ በህገመንግስት ያጸደቀውን የክልሎች ድንበር ተቀብሎና ተስማምቶ በሰላም የሚለያይ ብሄር ብሄረሰብ ይኖራል ብላችሁ የምታስቡ ስንት ናችሁ?

አዋሳን ዋና ከተማው ያደረገ ዛሬ የሲዳማ ዞን የተባለውን ድንበር ቋሚ ድንበሩ ያደረገ 55 ኛው የአፍሪካ ነጻ ሃገር፤ ፊንፊኔን ዋናው ከተማ ያደረገ ዛሬ ኦሮሚያ ክልል የያዘውን ዳር ድንበር የነጻይቱ 56ኛ የአፍሪካ ነጻ ሃገር፤ ባህር ዳርን ዋና ከተማው ያደረገ ዛሬ አማራ በሚባለው ክልልና ድንበር የታጠረ 57ኛው ነጻ የአፍሪካ ሃገር፤ መቀሌን ዋናው ከተማ ያደረገ ወልቃይት ጠገዴንና ሰሜን ወሎን ያካተተ ግዛት ያለው የትግራይ ሪፓብሊክ 58ኛ ነጻ የአፍሪካ ሃገር .... ወዘተ እያልን ከኢትዮጵያ ብቻ 80 ብሄር ብሄረሰቦች ወያኔ እንደሚለን ህገመንግስታዊ በሆነ መንገድ በሪፈረንደም፤ ካልሆነም ሌሎች እንደሚሉን በሃይል በነጻ መንግስትና ሃገርነት ራሳቸውን እያቆሙ የተባበሩት መንግስታትና የአፍሪካ ንድነት ድርጅት አባል ሃገራት ሆነው የሚመዘገቡበት እውነታ እውን ሲሆን የሚታየን ስንቶቻችን ነን?

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የብሄር ብሄረሰቦች ትስስርና አሰፋፋር በቀደሞው ሶቪየት ኢምፓየር፣ በዩጎዝላቪያና ቼኮዝላባኪያ ውስጥ እንደነበሩ ዛሬ የራሳቸው ነጻ የሆነ መንግስትና ግዛት እንደመሰረቱ ሃገሮች ቀርቶ በአጠገባችን በቅርቡ ራሳቸውን የቻሉ ሃገራት በሆኑት በኤርትራና በደቡብ ሱዳን ሞዴል ማየት ይቻላል ብላችሁ የምታስቡ ስንቶቻችሁ ናችሁ? ከዚህ እይታ አንጻር ለብሄረሰቦች የመገንጠል መብት የሰጠውን አንቀጽ 39 በመቀበልና ባለመቀበል በተቃዋሚዎች መሃል እንደትልቅ የልዩነት ነጥብ ተደረጎ የሚቀርበው ነጥብ እውን እንደሚባለው ትልቅ ነጥብ ነው? ህጋዊ በሆነም ሆነ ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ከዛሬይቱ ኢትዮጵያ ነገ የተባበሩት መንግስታት አባላት የሚሆኑ ሃገሮች ሲፈጠሩ ለማየት ቀርቶ ለማሰብ የሚወሳሰብብን ከሆነ በዚህ አንቀጽ ዙሪያ የጠፋውና ለሚጠፋው የፖለቲካ ልሂቆቻችን ጊዜና ጉልበት ምን ምክንያት ልንሰጠው ነው?

የመለያየት መንገድ ዛሬ በአንድነት ሆነን ከምንኖርበት ገሃነብ ሽህ ጊዜ የጠቆረ፣ በሰላምና በእፎይታ በብልጽግና የተሞላ መንገድ ሳይሆን በአጠቃላይ ውድመት፣ በደምና በእንባ የተሞላ ወደከፋ ገሃነም የሚወስድ መንገድ እንደሚሆን እያወቅን፣ ማን ከየት መጣ ማን የትሰፈረ፣ "የመገንጠል መብቴን

ትደግፋላህ አትደግፍም?” በሚሉ ልዩነቶች የጋራ ቤታችን የሆነችውን ኢትዮጵያ ለሁላችን የምትመችና የምትደላ ሁላችንንም በእኩልነት የምታስተናግድ አድርገን በጋራ እንዳንገነባ እንቅፋት ሲሆን ዝም ብሎ መመልከት እብደት አይሆንምን?

በተለይ ደግሞ ዛሬ በሃገራችን ወያኔን በሚቃወሙ የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ ያለው ገዥ የፖለቲካ አመለካከት የግለሰቦችንና የቡድኖችን መብት በማስከበር በእኩልነት ላይ የተመሰረተ በሃገራችን ውስጥ ያሉትን ባህሎችና ቋንቋዎች እምነቶች ስብጥር የተቀበለ፤ ይህንንም ስብጥር ለሃገራችን ልዩ ውበትና ጥንካሬ የሰጠ እሴት አድርጎ የሚያይ በሆነበት ወቅት በአንድነትና በመተባበር በቀላሉ ልናመጣው የምንችለውን የሁላችንንም መብት ያስከበረ ከውርደትና ከድህነት ያላቀቀ ሁኔታ እየተውን ውሉና መድረሻው ምን እንደሆነ፣ ለመሳካቱና ላለመሳካቱ ዋስትና በሌለው፣ ስብአዊና ቁሳዊ ወጪው ሁላችንም መክፈል ለማንችለው ኪሳራ ሊዳርገን እንደሚችል ነፍሳችን እየነገረችን ወዳለው የመለያየት ፖለቲካ ትኩረት በመስጠት ምናባዊ የነጻ ግዛት ድንበር እያካለልን፣ መናቆሩን ምን ይሉታል?

አንድነት የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን ከሁላችንም ህልውና፣ ደህንነት፣ መብት መከበር፣ ከድህነትና ከውርደት መውጫው፣ የሰላማችን፣ የእርጋታችን ብቸኛውና አቋራጭ መንገድ መሆኑን ልቡ የማይነግረው ማነው? ይህን እያወቅን ወደፊት በጋራ ስምምነት ከምንገነባው የጋራ ሃገር ጋር ግንኙነት በሌላቸው፣ ዛሬ ሁላችንንም በግልና በቡድን፣ በማህበረሰብና በብሄረሰብ ደረጃ ያለንበትን አዋራጅ ሁኔታ በማይቀይሩ ጉዳዮች ላይ ጊዜ ስናጠፋ መገኘታችን ነውር አይመስላችሁም።

ሌላው በአንድነት ጉዳይ ላይ ተመሳሳይነት ያለው አመለካከት መግባባት ላይ እንዳንደርስ አንዳንዶቻችን መሰናከል አድርገን የምናቀርባቸው ጉዳዮች በደቀቁ የታሪክ ኩነቶችና የታሪክ ተክለ ሰውነቶች ያሉንን የአመለካከት ልዩነቶች ነው። በሃገራችን ትንሹንም ትልቁንም የታሪክ ኩነትና የታሪክ ሰው እያነሳን ሁላችንም አንድ አይነት አመለካካት እንዲኖረን ማድረግ አይቻልም። በእንዲህ አይነቱ “በጥቁር ወይም ነጭ” መስፈርት የታሪክ ኩነቶችንና ግለሰቦችን እየሰፈሩ የሚደረስ ስምምነት የለም። “ቴዎድሮስ ጀግና ነበሩ” የምለው ሰው “የለም ቴዎድሮስ ጭፍን፣ ጨካኝ ሰው ነው” የሚል መልስ ቢሰጠኝ የኔን እይታ እንዲቀበል ለሽህ አመታት ብሞግተውም ላይቀበለኝ ይችላል። ሆኖም ግን “አዎን ቴዎድሮስ ጀግና ነበሩ፤ በዛውም ልክ ጨካኝ ነበሩ” ብለው። በአንድ ደቂቃ ውስጥ ከኔ ጋር ሊስማማ ይችላል። እንዲህ አይነቱ ስምምነት ሁለታችን በጋር ለምንሰራው በጣም ወሳኝ ስራ መደረስ ያለበት ስምምነት ከሆነ በዚህ መንገድ ተስማምቶ መጓዝ ተገቢ ነው። በጋራ መስራት ለምንፈልገው ስራ ስለ

ቴዎድሮስ ምንነት መስማማት አስፈላጊ ካልሆነ ልዩነታችንን ይዘን በጋራ እንሰራለን፤ ወዳልነው ስራ መሄድ እንችላለን። በጋራ ለመስራት ለምንፈልገው ጉዳይ ምንም ፋይዳ በሌላቸው የታሪክ ኩነቶችና ተከለ ሰውነቶች ላይ ለምን አንድ ወጥ አመለካከት አልያዝንም በሚል እልህ ከችግራችን መውጫ የሆነውን የሃገራችንን አንድነት እስከ ማፍረስ፣ በጋራ ተባብረን ለመስራት የሚያስገድደን ሁኔታ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንዳለን እስከንዘነጋ ድርስ አእምሯችንን እንስታለን።

በዚህ ጉዳይ ላይ አጼ ቴዎድሮስን በምሳሌነት አነሳሁ እንጂ በልሂቁ መሃል የከረሩ ሽኩቻዎች ምንጭ የሆኑ የታሪክ ኩነቶችና የታሪክ ሰዎች ቁጥራቸው ብዙ ነው። የሁላችንም ኩራት፣ የሁላችንም ጀግኖች ሊሆኑ የሚችሉ ቀደምቶቻችን አንድን የፖለቲካ ግብ ለማስፈጸም ስንል በቀረጽነው መነጽር በመመልከት የጋራ ታሪካችንን ብቻ ሳይሆን የራሴ የምንለውን ብሄር ብሄረሰብ ታሪክ ሳይቀር የሚያደኸይ እርምጃ እስከመውሰድ የደረስንበት ሁኔታዎች እንዳሉ ብዙ ምሳሌዎች መስጠት ይቻላል። ቁም ነገሩ ታሪክን ማእከሉ ያደረገ ክርክር የፈለገው ያህል በልዩነት የተሞላ ቢሆን በትናንት ታሪክ ታስረን ዛሬ ባርነትን ተቀብለን እንኑር፤ ለልጆቻችንም ባርነት እናውርስ፤ የሚል መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ ነው።

የራሳችንና የህዝባችን ስቃይና ውርደት ገደቡን አልፏል ብለን እናምናለን። ይህን የግፍ ዘመን ለማሳጠር በጋራ መስራት ይገባናል ብለው ከልባቸው ያመኑ የፖለቲካ ልሂቃን በጤነኛ አእምሮ ከዚህ መደምደሚያ ይደርሳሉ ብሎ ማሰብ የሚያዳግት ነው። ይህን ከተረዳን በአንዳንድ የታሪክ ኩነቶች ላይ ፈጽሞ ተመሳሳይነት ያለው ትርጉም መያዝ እንደማንችል፣ አብዛኛው የታሪክ ኩነትና ጭብጥ ቀደም ብዬ በአጼ ቴዎድሮስ ምሳሌ እንዳሳየሁት በድርድር የምንስማማባቸው ትርጉም ለመስጠት እንደምንችል፣ የተቀረው ሊያስማማን የሚችል የታሪክ ክፍል አድርገን በመውሰድ በታሪክ ዙሪያ መስመር አበጅተን የቀረውን ውዝግብ ለታሪክ ተመራማሪዎችና ተማሪዎች ትተን ወደፊት ለምን አንራመድም? የፖለቲካ ሰዎች በዚህ ጉዳይ ላይ ከዚህ የተለየ ሌላ ምን አማራጭ አላቸው? ያለፈውን ታሪክ እንደ ፍላጎታችን መልሰን ልንሰራው አንችልም። መጪውንም እንዳሻችን ልንሰራው ባንችልም፣ ትንሽም ቢሆን የዛሬው ትውልድ አሻራ እንዲኖረው ማድረግ እንችላለን። መጪው ታሪካችንን ሁላችንም በእኩልነት በጋራ የምንሰራው ነው። ሁላችንንም በጋራ ኩራት የሚያስተሳስር ታሪክ በማድረግ አዲስ ታሪክ መጻፍ እንችላለን። ይህ ታሪክ ደግሞ በአንድነት በመታገል በሁላችንም ጀርባ ላይ እንደአልቅት ተጣብቆ የነጻነት ህልማችንን፣ የተሻለ ቀን ተስፋችንን፣ ደማችንና ላባችንን

የሚመመጠውን የወያኔ ዘረኛ ጉጅሌ አስወግደን በቦታው ሁለተኛ አልቅቶች በህዝብ ጀርባ ላይ የማይወጡበትን ሁኔታ አመቻችቶ ማለፍ ነው። ሌላው ሁሉ ኣጉል ቅንጦትና መንደላቀቅ ነው።

ይህንን ካልኩ ሶስተኛውና አጭር ወደሆነው የንግግሬ ክፍል እሸጋገራለሁ።

## 3. የአንድነታችንን ፈተናዎች ለማለፍ መፍትሄው ምንድነው?

ለዚህ ጥያቄ መልሶቹን በንኡስ ክፍል አንድና ሁለት ላይ በዝርዝር እየሰጠሁ መጥቻለሁ። ይህን ጥያቄ እዚህ ላይ ለብቻው እንዳነሳ ያስገደደኝ ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት ተጨማሪ መፍትሄ ለማመላከት አይደለም። ቀደም ብዬ በመግቢያ ንግግሬ እንደጠቀስኩት ለአንድነት ችግራችን መፍትሄ የሚሆኑ ነገሮችን ማቅረብ ቢያቅተን ለችግሩ መፍትሄ የማይሆኑ ነገሮችን ማወቅ ሊከብደን አይገባም የሚለውን ጉዳይ በደንብ ልንመለከተው ይገባል የሚል እምነት ስላለኝ ነው። በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ “ወያኔን እንቃወማለን፤ ወያኔ የሃገር አንድነትና ህልውና ዋነኛው ቀበኛ ነው ብለን እናምናለን” ከሚሉ አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶችና የፖለቲካ ሰዎች አካባቢ የአንድነትን ፈተናዎች ለማለፍ በመፍትሄነት የሚሰነዘሩ ሃሳቦች የወያኔን የብተና ህልም የሚያሳኩ፤ ከአንድነት ውጭ ለችግራችን ሌላ መፍትሄ እንደሌለው በመረዳት መስመር መያዝ የያዘውን የብዙሃን እምነት ከገባባት ሃዲድ እንዲወጣ የሚያደርጉ ችግሮች እየሆኑ መጥተዋል የሚል እምነት አለኝ። ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት በአንድነት ጉዳይ ላይ የገጠመን ችግር ሳንወድ በግድ ተመሳሳይነት ወዳለው የአንድነት ግንዛቤ የሚወስደን፤ ያለዚህ ተመሳሳይ ግንዛቤ ጉዟችን የጋራ ውድመትን የሚያስከትል እንደሚሆን በአንድነት ጉዳይ ላይ ጥያቄ ያላቸውን ሃይሎች ሳይቀር ማሳመን የሚያስችል ወቅታዊ መረጃ እየተከማቸ በመጣበት ሃገራዊ ሁኔታ፣ ተጨባጭ አቅሙ ደካማ የሆነውን ጸረ ወያኔ ካምፕ የአንድነት እና የጸረ-አንድነት ሃይል በሚል ፍረጃ እርስበረሱ በጎሪጥ እንዲተያይ፤ ትኩረቱን ከዋናው የሃገር አንድነት ጠላት ከሆነው ከወያኔ ላይ አንስቶ አጋር ሊሆነው በሚችለው ወይም አጋሩ በሆነው የወገን ሃይል ላይ እንዲተኩስ የሚያደርግ አካሄድ የአንድነት ችግራችን መፍቻ ሊሆን እንደማይችል ማወቅ ሊከብዳቸው አይገባም። ይህን የሚያደርጉ የፖለቲካ ድርጅቶችና የፖለቲካ ተክለ ሰውነቶች ትናንት ፖለቲካ ውስጥ የገቡ ጮርቃዎች ሳይሆኑ በሃገራችን የፖለቲካ ታሪክ ለብዙ ዘመናት የተሳተፉ የፖለቲካው ጓዳና ጎርጓዳው ይጠፋቸዋል ብለን የማንገምታቸው መሆኑ የበለጠ ሁላችንንም ሊያሳስበን ይገባል። በተለይ ባሁኑ ወቅት ባሁኑ ዘመን ለምክክር ለድርድርና ለውይይት የተከፈተን በአንድነት ጉዳይ ላይ አጠቃላይ መግባባት ላይ ለመድረስ የተመቻቸ ሁኔታ ባለበት ወቅት “እኔ የአንድነት ሃይል ነኝ፤ በሶ የጨበጥኩ እንዳይመስልህ”

የሚል ዘመኑ ባለፈበት ፉከራና ቀረርቶ የአንድነት ችግራችን ይፈታል ብሎ ማሰብ እንዴት እንደቻሉ መጠየቅ ተገቢ ነው የሚል እምነት አለኝ።

ለመሆኑ "በአንድነት ጉዳይ ላይ ባለህ ኣመለካከት ዙሪያ ችግር አለኝ፤ እናም ካንተ ጋር በዚህ ጉዳይ ላይ መነጋገር እፈልጋለሁ" የሚልን ሃይል ማነጋገር ጸረ-አንድነት ድርጊት ተደርጎ የሚፈረጅበት መስፈርት ምንድነው? ለመሆኑ የኢትዮጵያ ፍቅር በምን ይለካል? ስለ ኢትዮጵያ አንድነት መፈክር ከሚያወርዱት ውስጥ ስንቶቹ ናቸው የመጨረሻዋን ጥይት ተጎንጭተው ቃላቸውን በተግባር ፈጽመው ያለፉት? በወያኔ የተጫነብን የአንድነት አደጋ መግለጫ በማውጣት፤ መፈክር በማውረድ፤ ከጎን ያሉት አጋሮች ላይ የቃላትና የፕሮፓጋንዳ ጥቃት በመሰንዘር መከላከል ይቻላል የሚል እምነት በምን ስሌት የተቀመረ ነው?

ለመሆኑ ከተግባር ውጭ በኢትዮጵያ አንድነት ዙሪያ ያሰፈሰፈውን አደጋ መቋቋሚያው መንገድ ምንድን ነው?

በግንቦት 7 እምነት የሃገር አንድነት ጉዳይ ቁማር የምንጫወትበት፤ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ቀረርቶ የምናሰማበት፤ የተወሰነ ደጋፊና አባል የተወሰነ የገንዘብና የቁስ ድጋፍ የምናገኝበት እንደ ተራ ሸቀጥ የሚታይ ጉዳይ ነው በሚል ጊዜያዊ ስሌት የምናነሳው ጉዳይ አይደለም።

ደጋግሜ እንዳነሳሁት አማራጭ የሌለው ከጨለማና ከሞት ወደ ብርሃንና ህይወት መውሰጃው መንገድ በሃገር አንድነት ጉዳይ ላይ መግባባት ስንደርስ ብቻ ነው ብለን ስለምናምን ነው። ይህ ስር የሰደደና ጥልቅ የአንድነት ትርጉም ነው በከፍተኛ ትእግስት፣ በከፍተኛ ቀናነት፣ ሰፊ የሰው ሃይል፣ ጊዜና ግብአት ድርጅታችን መድቦ ያለመታከት ጸረ-ወያኔ የሆነው ካምፕ በአንድነት ጉዳይ ላይ የጋራ አቋም እንዲይዝ እንድንሰራ የሚያስገድደን።

በጸረ ወያኔ ጎራ በተሰበሰበው ካምፕ ውስጥ የተሰባሰቡ ሃይሎችን በሃገር አንድነት ጉዳይ ላይ በመፈክርና በፉከራ ብቻ ወደ አንድነት ማምጣት እንደማይችል ልባቸው እያወቀ ሆነም አልሆነም እንበለው በሚል በፈንግጭው መርህ የሚመሩትን ራሳቸውን በቃል "የአንድነት ሃይሎች" በሚል ስንኝ የሚገልጹ ሃይሎች ድርጊታቸው የሀገሪቱን አንድነት ጠላቶች እጅ የሚያጠናክር እንደሆነ ልንነግራቸው ይገባል። **ጊዜው የሚጠይቀው፤ ኢትዮጵያችን ለአንድነቷ ኣሁን በተጨባጭ የምትሻው፤ በባዶ ፉከራ የሚያቅራሩላትን ሳይሆን ኣንድነቷን ለማስጠበቅ በተግባር የሚንቀሳቀሱትን፤ ያኮረፉ ልጆቿን በብልህትና በሆደ ሰፊነት የሚሰበስቡትን፤ አንድነቷ ዘላቂ በሆነ የዜግነት እኩልነትና በፍትህ መደላድል ላይ ለማስቀመጥ የሚያስችል**

**የጋራ ግንዛቤ ለመፍጠር ከልባቸው በተግባርና በብልሀት የሚንቀሳቀሱ ልጆቿን ነው።** በዚህ ስሌት ደግሞ ግንቦት 7 ህዝባችን የገባበትን አጣቢቂኝ በመረዳት የአገራችን የኢትዮጵያን ዘላቂ አንድነት በተግባር ለማስጠበቅ ከሚንቀሳቀሱት የተግባር ድርጅቶች ዉስጥ ግንባር ቀደሙ ድርጅት ነዉ ብዬ በድፍረትና በሙሉ ልብ መናገር የምችል ይመስለኛል።

ግንቦት 7 በአንድነት ጥያቄ ላይ ያለውን አቋምና ተግባራዊ እንቅስቃሴ በአግቦ እንኳን ለመጠየቅ የሚሞክሩ ሀይሎች እዚህ አሜሪካን አገር የፕሬዘዳንት ኦባማን ዜግነት ከሚጠይቁ አክራሪ የፖለቲካ ሰዎች (the birther movement) ጋር የሚያመሳስላቸው ነገር አለ። ሁለቱም መሰረታዊና ጥልቅ ሀሳብን የሚጠይቁ አገራዊ ችግሮች ባሉበት ሁኔታ ምንም እውነትም ሆነ ተግባራዊ ፋይዳ የሌለው፤ አይገባውም ብለው በሚንቁት ህዝብ መሀል ጊዜያዊ ድጋፍ ለማግኘት ብቻ ሲባል የሚነሱ ኦባማ እንዳለው "የፖለቲካ የማስመሰያ ቀልድ ጊዜ" (political silly season) ገላጮች ብቻ ናቸው። አሜሪካኖቹ እንዲህ አይነቱን ከንቱ ጨዋታ መቋቋም የሚችል ተቋማት የገነቡ በመሆኑ በእንዲህ ኣይነት ተራ ፖለቲካ ብዙም አይጎዱም። እኛ ላለንበት ችግር ጥልቀትና እንዲህ አይነት ከንቱ መላፋት በትግላችንና በህዝባችን ላይ ከሚያደርሰው የሞራል ማዳከም ኣንጻር ስናየው ግን ዝም ብለን የምናልፈው ሊሆን ኣይገባም። ዛሬ ኢትዮጵያችን ካለችበት ችግር ኣንጻር ምንም ተግባራዊ ፋይዳ በሌለው ያውም በኣገር ኣንድነት ጥያቄ ላይ ምንም የኣመለካከት ልዩነት ሳይኖር "የኣንድነት ሀይሎችና" "የኣንድነት ሀይል ያልሆኑ" በሚል ከንቱ መላፋት ላይ የፖለቲካ ወረታቸውን የሚያሚጥጡ ሀይሎችን "የቀልድና የወሬ ጊዜው ኣልፎኣል፤ ኣሁን የተግባር መፍትሄ የሚሰጥበት ጊዜ ነው፤ ኣቅሙ ካላችሁ፤ የሚሰራ የተግባርና የተሻለ መፍትሄ ይዛችሁ በስራችሁና በድካማችሁ ፍሬ ሊሰጥ የሚችል የተግባር እንቅስቃሴ ውስጥ ግቡ። ሁላችንም ያለንን አቅም ለትግሉ ስኬት በሚውል ስራ ላይ ካዋልነው፤ሁላችንም በግልም፤ በድርጅትም፤ በተለይ ደግሞ እንደ ያንድ አገር ልጆች የውጤቱ ተጠቃሚዎች እንሆናለን። ሌላውን በመንተትና በመጣል የሚገኘው "ትርፍ" ግን ግፋ ቢል ሁሉም የሚወድቅበትን ሁኔታ ማመቻቸት (ቆምኩለት የሚሉትን አላማ ጨምሮ) እንጂ ምንም አወንታዊ ትርፍ እንደሌለው የቅርብ ጊዜ ታሪካችን ሊያስተምረን ይገባል።

ከዚህ ውጪ ግን የአገራችን አንድነት እውነተኛ ጠንቅ የሆነውን፤ ኣገራችንን በዘርና በሀይማኖት ብቻ ሳይሆን በሀይማኖቶች ውስጥም ገብቶ መከፋፈልን የሚፈጥረውን፤ የሀገሪቱን ሀብት በብቸኝነት ተቆጣጥሮ መሬቷን እየሸነሸነ ለባእዳን እየቸበቸበና ገሚሱን በችሮታ እየሰጠ ያለውን፤ ሁሉንም የሀገሪቱን ህዝብ ኣዋርዶ እየገዛ ያለውን የወያኔ ገዢ ጉጅሌ ለመጣል ከምራቸው ከተነሱ፤ የሀገሪቱን አንድነት በተደላደለ የዜግነት እኩልነት ላይ ለማስቀመጥና ለዚህም ወሳኝ የሆነውን ያልተማከለ ዴሞክራሲያዊ ስርኣት ለመገንባት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ ከቆረጡ (በትግል ስልት ዙሪያ ወይንም በሌሎች ዝርዝር

ጉዳዮች ላይ ያሉ ልዩነቶች እንደተጠበቁ ሆነው) ማናቸውም በዘውግም ሆነ በህብረ_ዘውግ ደረጃ ከተደራጁ ኢትዮጵያዊ ሀይሎች ጋር ተመካክሮ ለመስራት፤ ለመቀናጀት፤ የማህበረሰባችንን ኣንድነት በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ በሚኖሩ ዜጎች ዘንድ ለማስጠበቅ በሚደረግ እንቅስቃሴ፤ ኣልፎም ትግሉን ኣቀናብሮ በጋራ ለማስኬድ ግንቦት 7 ምን ጊዜም ዝግጁ መሆኑን ብቻ ሳይሆን ኣማራጭ የሌለው ብቸኛ መንገዳችን ነው ብለን ከልባችን እንደምናምን በዚህ ኣጋጣሚ በድጋሚ ማስረገጥ እንፈልጋለን። ይህንንም በተግባር ሌት ተቀን እየሰራንበት እንደሆነ ማሳወቅ እንፈልጋለን። ከዚህ በተጨማሪም ጸረ_ወያኔ ከሆኑ ማናቸውም ኢትዮጵያዊ ሀይሎች ጋር፤ ምንም አይነት የአመለካከት ልዩነት ይኑረን፤ አላስፈላጊ የሆነ እንካሰላንትያ ውስጥ ላለመግባት ድርጅታችን ከተቋቋመ ጀምሮ የወሰነውንና በተግባርም እየፈጸመ ያለውን ውሳኔ አሁንም እያከበረ እንደሚቀጥል፤ ይህም ወደፊት እንዲሆን ለምንፈልገው የጋራ ትግል አስፈላጊውን አወንታዊ የስነልቦና ድባብ ስለሚፈጥር ሁሉም የፖለቲካ ሃይሎች ከምር እንዲወስዱትና እንዲተገብሩት በአጽንኦት እንጥይቃለን።

አመሰግናለሁ